Alexandria City Public Schools

# ACPS የአሜሪካ የማዳን እቅድ (ARP) የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የድንገተኛ ጊዜ እርዳታ (ESSER) ፈንድ III

## ለሕዝብ አስተያየት ለመስጠት ያቅዱ



**ጁላይ 2021**

## ከዋና ተቆጣጣሪ Dr. Hutchings የተላከ ደብዳቤ

በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት የትምህርት ቤታችን ሕንፃዎች ከተዘጉ ጀምሮ፣ ACPS ለተማሪዎች እና ለቤተሰቦች የተለያዩ የትምህርት ዕድሎችን ማቅረቡን ቀጥሏል። ACPS ተማሪዎች እና ቤተሰቦች በአስቸጋሪው ጊዜ የቴክኖሎጂ፣ የመማሪያ ቁሳቁሶች፣ የትምህርት ሃብቶች፣ ምግቦች እና የድጋፍ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ አድርጓል። የተማሪዎችን እና የሰራተኞቻችንን ደህንነት በግንባር ቀደምትነት እየያዝን ከወረርሽኙ ለማገገም ጉዟችንን ስንቀጥል፣ ACPS ወደ 2021-2022 የትምህርት ዘመን እየተቃረበ ያለው ማህበረሰባችንን “ለማዳን፣ ለማቆየት እና ዳግም ለማነቃቃት” ተልዕኮን በማንገብ ነው። በ **ACPS 2025 ውስጥ የተቀመጡትን ተልዕኮ፣ ራዕይ እና ዋና እሴቶች እውን ለማድረግ በምናደርገው ጥረት ወደፊት እየተጓዝን ነው፡- ፍትሃዊነት ለሁሉም** ስትራቴጂክ የዘር እኩልነትን በስራችን ማዕከል ውስጥ የያዘ ሲሆን እያንዳንዱ ተማሪ በ 21ኛው ክፍለ ዘመን ስኬታማ ለመሆን የሚያስፈልጉ ክህሎቶች እንዲኖሩት ለማዘጋጀት ይጥራል። ለዚህ ሥራ ዋነኛው ትኩረት በወረርሽኙ የተጎዱትን ቁልፍ በታዎችን ለመቅረፍ እቅዳችን እና አፈፃፀማችን ነው - የመማር መቀነስ፣ ማህበራዊ እና ስሜታዊ ተጽዕኖዎች፣ ዲጂታል ክፍፍል እና በሰራተኞች ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ።

እነዚህን ጥረቶች ለማገዝ፣ ACPS በ ኮቪድ-19 ወረርሽኝ እና ከዚያ ባለፈ የመንግስት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ት/ቤቶችን ለመደገፍ ወጪያቸው በፌደራል መንግስት የሚሸፈኑ ፕሮግራሞችን በማግኘቱ እድለኛ ነው። የእነዚህ ፕሮግራሞች አጠቃላይ ዓላማ ኮቪድ-19 ቨርጂኒያ ውስጥ በሚገኙ የመጀመሪያ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ያሳደረውን እና እያሳደረ ያለውን ተጽዕኖ ለመቅረፍ ነው።

- የ CARES ድንጋጌ በማርች 27/2020 ወደህጉ እንዲገባ ተፈርሟል። የ CARES ድንጋጌ የ 30.75 ቢሊየን ዶላር የትምህርት ማረጋጊያ ገንዘብን ከሰስት አካላት ጋር ያጠቃልላል፡- የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ (ESSER) ፈንድ፣ የሃገረ ገዥው የአስቸኳይ ጊዜ የትምህርት እፎይታ (GEER) ፈንድ እና የከፍተኛ ትምህርት የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ (HEER) ፈንድ።
- የ Coronavirus Response and Relief Supplemental Appropriations (CRRSA) ሕግ የተፈቀደው በዲሴምበር 2020 ነው። የ CRRSA ድንጋጌ ተጨማሪ 82 ቢሊየን ዶላር የትምህርት ማረጋጊያ ገንዘብን ያካትታል። የ CRRSA Act ESSER II እና GEER II ፈንድ ከ CARES ሕግ ፈንድ ጋር ተመሳሳይ ለሆኑ ፕሮግራሞችና ተግባራት ሊውል ይችላል።
- የ American Rescue Plan (ARP) ሕግ የጸደቀው በማርች 2021 ነበር። የ ARP ድንጋጌ ተጨማሪ 122 ቢሊዮን ዶላር በ ESSER III ፈንድ ውስጥ ያካተተ ሲሆን ይህም ከ ESSER I እና ESSER II ጋር ተመሳሳይ ለሆኑ ፕሮግራሞች እና ተግባራት ሊያገለግል ይችላል።

የ ACPS የፌዴራል ኮቪድ-19 የእርዳታ ገንዘብ ድጋፍ እስካሁን ድረስ በግምት 56.7 ሚሊዮን ዶላር ያህል ነው። የ American Rescue Plan (ARP) ድንጋጌ የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ (ESSER) III ፈንድ ለ ACPS የመደበው ገንዘብ 34.8 ሚሊዮን ዶላር ነው። ድልድሉ የተመሰረተው በ ACPS ርዕስ 1፣ ክፍል ኤ፣ የፌዴራል የሒሳብ ዓመት 2020 ፈንድ አንጻራዊ ድርሻ ላይ ነው። ከጠቅላላው ገንዘብ ውስጥ ሁለት ሦስተኛው ከኤፕሪል 30/2021 ጀምሮ ዝግጁ ሆኖ ይገኛል፤ የቀረው ሶስተኛው ደግሞ በግዛት ደረጃ የማመልከቻ ሂደት ሲጠናቀቅ በዚህ ሴፕቴምበር 2021 ዝግጁ ይሆናል። የ ARP ሕግ ESSER III ፈንድ የገንዘብ ድጋፍ መጠየቂያ ማመልከቻውን እና የድጋፍ ሰነዶቹን ለማግኘት የሚያስችሉት መመሪያዎች ለት/ቤት መምሪያ የፌደራል ወረርሽኝ እፎይታ ፕሮግራሞች በኢሜይል ተልኳል። ማመልከቻዎች እስከ ሴፕቴምበር 1/2021 ድረስ ገቢ ይደረጋሉ።

በ ARP ድንጋጌ ክፍል 2001 (e) በ ESSER I እና ESSER II መሠረት ሁሉንም የተፈቀዱ የፈንድ አጠቃቀምን ያካተተ ሲሆን **በማስረጃ ላይ የተመሠረተ ጣልቃ ገብነት በመተግበር የመማር እጦትን ለመቅረፍ የሃያ በመቶ (20%) ክፍፍል ቀመር ገንዘብ እንዲቀመጥ ይጠይቃል** እንደዚሁም እነዚህ ጣልቃ-ገብነቶች ለተማሪዎች ማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና አካዳሚክ ፍላጎቶች ምላሽ የሚሰጡ እና የኮቪድ-19 ያልተመጣጠነ ተፅእኖን በበቂ ሁኔታ ባልተወከሉ የተማሪ ቡድኖች (እያንዳንዱ ዋና የዘር እና የጎሳ ቡድን፣ ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ቤተሰቦች የመጡ ልጆች ፣ የአካል ጉዳተኛ ልጆች፣ የእንግሊዝኛ ተማሪዎች)፣ ፆታ፣ ስደተኛ ተማሪዎች፣ የቤት አልባነት ያጋጠማቸው ተማሪዎች እና በአሳዳጊ እንክብካቤ ውስጥ ያሉ ልጆች እና ወጣቶች) የሚመክቱ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። እንደ ESSER I እና ESSER II ሁሉ፣ እያንዳንዱ ወጪ የ ኮቪድ-19 ተጽዕኖዎችን እንዴት እንደሚቀርፍ መግለጫ በፕሮግራሙ ማመልከቻ ውስጥ መቅረብ አለበት።

የ ARP የገንዘብ ድጋፍን ለማግኘት ሌላኛው መስፈርት እያንዳንዱ የትምህርት ቤት መምሪያ የ ESSER III የቀመር ገንዘብ ድጋፍን በተቀበለ በ 30 ቀናት ውስጥ ደህንነቱ በተጠበቀ መንገድ ወደ ፊት ለፊት ትምህርት ለመመለስና አገልግሎቶችን ለማስቀጠል ያለውን ዕቅድ በድረ ገጹ ላይ በይፋ ማቅረብ አለበት። የትምህርት ቤት መምሪያው ዕቅዱን በይፋ ከማቅረቡ በፊት **በእቅዱ ላይ የህዝብ**

**አስተያየት ማሰባሰብና ይህንኑ ጁን 18፣ 2021 ላይ በኦንላይን ዳሰሳ ጥናት የተጠናቀቀውን አስተያየት ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል**። እያንዳንዱ የትምህርት ቤት መምሪያ የ ESSER III ቀመር የገንዘብ ድጋፍ በተቀበለ በ 90 ቀናት ውስጥ የገንዘቡን አጠቃቀም ዕቅድ በይፋ በድረ ገጹ ላይ ማቅረብ አለበት። ዕቅዱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር መዘጋጀት ያለበት ሲሆን፣ የተሰጠውን የህዝብ አስተያየትም ታሳቢ ማድረግ አለበት።

የ ARP ሕጉ ለ 2022 እና 2023 የበጀት ዓመቱ የፍትሃዊነት መስፈርቶችን በአካባቢያዊ የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) ማስቀጠልን ያካትታል። አንድ የት/ቤት መምሪያ የ ESSER III የቀመር ገንዘብን ለመቀበል በ 2022 ወይም በ 2023 የበጀት ዓመት ውስጥ ለማንኛውም ከፍተኛ ድህነት ላለበት ት/ቤት ለእያንዳንዱ ተማሪ የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍን (ከግዛት አቀፍና ከአካባቢ የገንዘብ ድጎማ) በት/ቤት መምሪያው ስር ያሉ ሁሉም ት/ቤቶች የሚሰጣቸው የገንዘብ ድጋፍ ላይ የሚደረግ ቅነሳ መጠን በሁሉም ት/ቤቶች ውስጥ ለተመዘገቡ ተማሪዎች ቁጥር ሲካፈል ከሚመጣው ቁጥር በታች መቀነስ አይችልም ወይም ከፍተኛ ድህነት ባለበት ት/ቤት ውስጥ የእያንዳንዱን ተማሪ፣ የሙሉ ጊዜ ሰራተኞች ቁጥርን ሁሉም ት/ቤቶች ውስጥ ያሉ ሰራተኞች ቁጥር በሁሉም ት/ቤቶች ውስጥ ለተመዘገቡ ልጆች ቁጥር ሲካፈል ከሚመጣው ቁጥር በታች መቀነስ የለበትም። የ ESSER III ቀመር ገንዘብ ከ ESSER I እና ESSER II ገንዘብ ጋር በአንድ ጊዜ ተመላሽ ሊደረግ ይችላል።

እስከዛሬ ድረስ በመላው የድርጅቱ እና በማህበረሰቡ አጋር አካላት ውስጥ የተሰማሩ ባለ ብዙ ተግባር ሰራተኞችን ያቀፉ የትኩረት አካባቢ ቡድኖች በማህበራዊ፣ በስሜታዊ ድጋፍ እና በእኩልነት፣ በአካዳሚክ ትምህርት፣ በቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት፣ በኮቪድ-19 ቅነሳ ፕሮጀክቶች፣ እና በእኛ የሰው ሃይል ካፒታል ፍላጎቶች ላይ እያተኮሩና እና በአብዛኛዎቹ ሁኔታዎችም ትኩረታችንን እያስቀጠሉ ነው።

EQUITY FOR ALL 2025

**ACPS 2025 ስትራቴጂክ ግቦች**

የስርዓት አሰላለፍ
የመመሪያ ልቀት
የተማሪ ተደራሽነት እና ድጋፍ
ስልታዊ የግብዓት አመዳደብ
የቤተሰብና ማህበረሰብ ተሳትፎ

| ማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ አካዳሚያዊ ትምህርት (SEAL) | የኮቪድ 19 መቀነሻ ፕሮጀክቶች | የሰው ሐይል ካፒታል ፍላጎቶች | የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት |
|---|---|---|---|

እነዚህ ቡድኖች ሐምሌ 27/2021 እቅዳችንን ይፋ ለማድረግና ነሐሴ 3/2021 በተካሄደው ህዝባዊ ውይይት ላይ የህዝብ አስተያየት ለመጠየቅ እየተሰበሰቡ፣ ቅድሚያ እየሰጡ፣ ዕቅድ እያዘጋጁና ዝግጅት እያደረጉ ነው። ከሴፕቴምበር 1/2021 ቀነ ገደብ በፊት ኦገስት 25/2021 ላይ የ ACPS ማመልከቻን የማቅረብ ዓላማ አለን።

እርግጥ ነው፣ ለትግበራችን እና ለተጠያቂነት ሕዝባዊ ተሳትፎ በጣም ወሳኝ ነው። በማመልከቻው ሂደት በሙሉ እና በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት የትግበራ እና የአፈፃፀም ምዕራፎች ውስጥ በእቅዶቻችን ላይ ወቅታዊ ግምገማዎችን እናካሂዳለን፣ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜም ለህብረተሰቡ ፍላጎቶች አግባብነት ያላቸው መሆናቸውን ለማረጋገጥ እንከልሳለን። የሕግ ተገዥነትን ለመከታተልና የአሌክሳንድሪያ ከተማ ትምህርት ቤት ቦርድ፣ የቨርጂኒያ ትምህርት መምሪያ እንዲሁም የዩኤስ ትምህርት ሚኒስቴር የሪፖርት ማቅረቢያ መስፈርቶችን ለማሟላት የሚያስችሉንን ሂደቶች አዘጋጅተናል።

## ESSER III ከስትራቴጂክ ዕቅዳችን እና ከዳግም መክፈቻ እቅዳችን ጋር የሚጣጣመው እንዴት ነው?

ACPS በ American Rescue Plan (ARP) ሕግ የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ (ESSER) III የግራንት ፕሮግራም አማካይነት በግምት 34.8 ሚሊዮን ዶላር ያገኛል። የ ARP ESSER III ፈንድ ዓላማ የትምህርት ቤቶችን ዳግም ለመክፈት እና ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ስራቸውን ለማስቀጠል እገዛ ማድረግና ከቪድ-19 በተማሪዎች ማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ አካዳሚክ እና የአእምሮ ጤንነት ፍላጎቶች ላይ ለሚያደርሰው ተጽእኖ መፍትሄ ለመስጠት ነው። ይህ ፈንድ ከ2024 እስከ 2025 የትምህርት ዘመን ለእኛ ዝግጁ ይሆናል።

መምሪያችን የ ESSER III ዕቅዳችን የሚገነባበት ጠንካራ መሰረት ያለው ሲሆን፣ ተልዕኳችንም ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ወሳኝ ሆኗል፡

***የ ACPS ተልዕኮ፡ ተማሪዎችን በማነሳሳት እና የትምህርቱ እንቅፋቶችን በማቃለል ስኬትን ማረጋገጥ።***

የ ESSER III ፈንዶቻችን በ **ACPS 2025 ውስጥ የተዘረዘሩትን ግቦች ለማሳካት ጥቅም ላይ ይውላሉ፡ እኩልነት ለሁሉም**። ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ትምህርት መሳተፋቸውን፣ ትምህርታቸውን ለማሳደግ የሚያስፈልጉትን የትምህርት ግብዓቶችን ማግኘታቸውንና ደህንነታቸው በተጠበቀ፣ ወዳጃዊ እና እንግዳ ተቀባይ በሆኑ አካባቢዎች ውስጥ መሳተፋቸውን እናረጋግጣለን። የዕድሎችን እና የስኬት ክፍተቶችን ለሚያስወግዱ እንዲሁም ሁሉም ተማሪዎች ለኮሌጅ፣ ለወታደራዊ አገልግሎት፣ ለሙያ እና ለህይወት ዝግጁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ለሚያረጋግጡ መምሪያ አቀፍ ቀዳሚነቶችና ፕሮግራሞች ገንዘብ እንመድባለን።


የስትራቴጂክ ዕቅድ ጥረታችን እና ዳግም የመክፈት እቅዳችን አካል በመሆኑ፣ ከ ACPS ሠራተኞች፣ ከአመራር፣ ከወላጆች፣ ከትምህርት ቤት የቦርድ አባላት እና ከዋና ዋና የከተማ እና የማህበረሰብ ድርጅቶች ተወካዮች አውድ ሰብስበናል። በሚቀጥሉት ወራቶች የቤተሰባችን እና የማህበረሰብ ተሳትፎን የበለጠ ለማስፋት አቅደናል፣ ስለሆነም ይጠብቁን። ቀጣይነት ያለው የተሳትፎ እና የክትትል እቅዳችን ድርጊቶቻችን ከከተማ እና ከግዛት ኤጀንሲዎች ከሚሰጡት ምክረ ሃሳቦች፣ ከአካባቢው የድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች እቅዶች እና በዩናይትድ ስቴትስ የትምህርት ሚኒስቴር ከተለቀቁት ብሔራዊ መመሪያዎች ጋር የሚስማማ እንደሚሆን እርግጠኞች ነን።

ስለነዚህ ስትራቴጂካዊ ዕቅዶች እና የተወሰኑ እርምጃዎች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ ከዚህ በታች የተገናኙትን የመነሻ ሰነዶችን እና ተያያዥ ማቴሪያሎችን ይመልከቱ።




**ACPS 2025: እኩልነት ለሁሉም**

*ሁሉም መረጃዎች በ[ስትራቴጂክ ዕቅድ](#) የመነሻ ገጻችን ላይ ማግኘት ይቻላል።*




**የትምህርት ዕቅድ ቀጣይነት 6.0**

*ሁሉም መረጃዎች በእኛ [ደረጃ በደረጃ የዳግም መግቢያ ዕቅድ](#) ገጾች ላይ ማግኘት ይቻላል።*

## የትኩረት መስክ
# ማሕበራዊ፣ ስሜታዊ እና አካዳሚያዊ ትምህርት

የዕድሎች እና የስኬት ክፍተቶችን ለማስወገድ ያለን ቁርጠኝነት አካል እንደመሆኑ መጠን፣ የትምህርት እንቅፋቶችን በሚቀንሱ ከፍተኛ ጥራት ባላቸው የትምህርት አሰጣጥና እና ፕሮግራሞች ተደራሽነትን እና ተሳትፎን የማረጋገጥ እቅዳችን ላይ አተኩረናል። ት/ቤቶቻችንን ዳግም መክፈት ከዚህ በፊት ታይተው የማይታወቁ ተግዳሮቶች እያጋጠሙም ቢሆን ተለዋዋጭነትን የመቀበል ፍላጎትን እንደሚያካትት እንገነዘባለን። ስለዚህ፣ በቀድሞው የ ESSER II የገንዘብ ድጋፍ እና በ 22 የበጀት ዓመት የተጠናቀረ የበጀት ሂደት አማካይነት፣ ለተማሪዎች፣ ለሠራተኞች እና ለቤተሰቦች ወሳኝ የሆኑ የማስተማሪያ ፕሮግራሞችን እና የተማሪ ድጋፍ አገልግሎቶች ፕሮግራሞችን ወጪ ሸፍነናል።

- ከትምህርታችን እና ከማስተማር እና ከመማር ማዕቀፋችን እና ባለብዙ ደረጃ ድጋፍ ስርዓቶቻችን (MTSS) ጋር የተጣጣመ የማስተማሪያ ድባብና የመማሪያ አካባቢን መግለጽ።
- በ 2021-2022 የትምህርት ዓመት በአካል በሚሰጡ የመማሪያ ዕድሎች ለሚፈጥሩት ተግዳሮቶች እና ልዩ እምቅ አቅም በሙያዊ ትምህርት እና የጤንነት ፕሮግራሞች አማካይነት ሰራተኞችን ማዘጋጀት።
- በ ACPS ተቋማትና ከዚያም ባለፈ በሚሰጡ የተራዘመ የድጋፍ አገልግሎቶች እና ፕሮግራሞች አማካይነት የተማሪዎቻችን እና ቤተሰቦቻችንን ማህበረ-ስሜታዊ ጤንነት መደገፍ።

የ ESSER III ገንዘብን ለመጠቀም በምናቅድበት ወቅት፣ ከፍተኛ ጥራት ያላቸው ፕሮግራሞችን በመተግበር፣ የፕሮግራሞችን ውጤታማነት በማሳደግና ድጋፍ ለሚያሻቸው ተማሪዎችና ቤተሰቦች ቀጥተኛ ድጋፍ በመስጠት ሁሉንም ሰራተኞች የማገዝ ዓላማ አለን።

- የትምህርት እገዛ፣ የተራዘመ ቀን እና የበጋ አካዳሚክ አካዳሚ ስኬት (SAAS) ን ጨምሮ የተራዘሙ የመማሪያ ዕድሎችን ቀጣይነት መፍጠር። ተጨማሪ የተራዘመ ቀን አገልገሎቶችን ትኩረት ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ማድረግ።
- የደረጃ 1 ማስተማሪያን እና ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች እና ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የማስተማሪያ ፕሮግራምን በመደገፍ ላይ ያተኮሩ ዋና ዋና ማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና አካዳሚያዊ የትምህርት ተነሳሽነቶችን (በአካል እና በቨርቹዋል ትምህርት) ውጤታማነት ለመገምገም የክትትልና ግምገማ ስርዓት መዘርጋት።
- ባለ ብዙ ደረጃ የድጋፍ ስርዓቶች ላይ የት/ቤት መሪን እና የሰራተኞችን ብቃት መገንባትን መቀጠልና በመማሪያ ክፍል፣ በት/ቤት እና በዲስትሪክት ደረጃ የዳታ ትንተና እና ሪፖርት ማድረጊያ መሳሪያዎችን መገንባት።
- በስሜቶች፣ በግንኙነቶች እና በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ትምህርቶችን ወደ ዋናው ሥርዓተ-ትምህርት ለማካተት ማህበረ-ስሜታዊ ሥርዓተ ትምህርታችንን (RULER) ማስፋፋት።
- በተማሪዎች ጥንካሬዎች ላይ ያተኮሩ ሁለንተናዊ ማህበረ-ስሜታዊ የማጣሪያ መሳሪያዎችን መተግበር።
- በማስረጃ ላይ የተመሰረቱ ልምዶችን መጠቀምን ጨምሮ መምህራንና ሰራተኞች የጭንቀት ምልክቶችን እና የአእምሮ ጤንነት ችግር ሊኖርባቸው የሚችሉ ተማሪዎችን ለመለየት እንዲችሉ አስተማሪዎችን እና ሰራተኞችን ማዘጋጀት።

ለ 2021-2022 የትምህርት ዘመን የታቀደውን የማሕበራዊ፣ ስሜታዊ እና አካዳሚያዊ የፕሮግራም ዝግጅታችንን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የእኛን የትምህርት ዕቅድ ቀጣይነት ይመልከቱ።

## የትኩረት መስክ
# የኮቪድ 19 የማቃለያ ፕሮጀክቶች

የፋሲሊቲዎችና የኦፕሬሽን ቡድናችን የ ACPS ተቋማትን በትምህርትና ትብብር፣ በደስታና ድጋፍ ለመሙላት እየተዘጋጀ ባለበት ወቅት፣ አዎንታዊ የሆነ የቤት ውስጥ የአየር ድባብ ከመፍጠርና ይዞ ከማቆየት ጎን ለጎን የጀርሞች/ቫይረሶችን ስርጭት ለማቃለል አስፈላጊ እርምጃዎችን እየወሰድን ነው።

መሪዎችና የት/ቤት ቡድኖች ተማሪዎችን በሙሉ ሰዓት ተማሪነት ለመቀበል በሚዘጋጁበት ወቅት እነርሱን ለመደገፍ ቡድናችን ገንዘብ መድቧል። በዝግጅት ስራ ውስጥ የሚካተቱት ተገቢ የደህንነት እና የአቅጣጫ ጠቋሚ ምልክት፣ እንዳስፈላጊነቱ ለተማሪዎች እና ለሠራተኞች የግል ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያዎችን ማቅረብ፣ የተሻሻለ ጽዳትን ማስቀጠል፣ አዎንታዊ የቤት ውስጥ አየር ጥራት እና የአየር ማናፈሻ መኖር እንዲሁም የተቋሙን ተደራሽነት እና አጠቃቀም በተመለከተ የደህንነት ፕሮቶኮሎችን ማዘመን ናቸው።

በ ESSER III ፈንድ አማካይነት፣ ሁሉም ተቋማት በቂ የቤት ውስጥ አየር ጥራት እንዲኖራቸው ለማስቻል መሠረታዊ ጥገናዎች እና ማሻሻያዎች ላይ ማተኮር እንችላለን። ከእነዚህ ማሻሻያዎች እና ለውጦች ውስጥ አብዛኞቹ ACPS የረጅም ጊዜ የጥገና ወጪዎችን በመቀነስ ይበልጥ ተስማሚ በሆነ የበጀት ሁኔታ ውስጥ እንዲሆን ያስችሉታል። ለዚህ የገንዘብ ድጋፍ ከለየናቸው አንዳንድ ተነሳሽነቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡

- ዓመቱን ሙሉ ከታለሙ ሙከራዎች ጋር ከትክክለኛው የአየር ማናፈሻ መመሪያዎች ጋር በተያያዘ የማሞቂያ፣ የአየር ማናፈሻ እና የአየር ማቀዝቀዣ (HVAC) ስርዓቶች ውጤታማ እና የሚሰሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ።
- ሻጋታዎችን፣ አለርጂዎችን እና ወደ ተቋማት የሚገቡ ተባዮችን ለመከላከል እንዲቻል የሕንጻው ውጫዊ አካል አየር የማያሳልፍ መሆኑን ማረጋገጥ።
- የሚመከር እና ቀጣይነት ያለው የመከላከያ ጥገናን ጨምሮ በእኛ የተቋማት ሁኔታ የምዘና ውጤቶች ላይ በመመርኮዝ አስፈላጊ የውስጥ እና የውጭ አካላት ላይ ጥገናዎችን ማካሄድ።

ስለ ዕቅዶቻችን ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የፋሲሊቲዎች እና ኦፕሬሽን መምሪያችንን የመነሻ ገጽ ይመልከቱ።

## የትኩረት መስክ
# የሰብአዊ ካፒታል ፍላጎቶች

ት/ቤቶቻችንን እንደገና ለመክፈት እና በስትራቴጂክ እቅዳችን ውስጥ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት፣ ለሁሉም አካታች የስራ ሁኔታን በመገንባት ነባር ሰራተኞቻችንን የምንደግፍባቸውን መንገዶች እያሰፋን ነው። ቡድናችን የስትራቴጂክ እና የኦፕሬሽን እቅዳችንን ለማሻሻል፣ የትብብር ግንኙነቶችን ለመፍጠር እና ግንኙነቶችን ለማሳደግ እንዲሁም ጥቅማ ጥቅሞቻችን የገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ለማድረግና ክፍያው ፍትሃዊ እንዲሆኑ ለማድረግ ቃል ገብቷል።

በ ESSER III ፈንድ አማካይነት፣ የሰራተኞችን ደህንነት እና ማቆያ ፕሮግራሞችን በማስፋት ላይ እንዲሁም ግዙፍ እና የተለያዩ የአቅርቦት መስመርን ለመገንባት የምልመላ ጥረታችንን በመጨመር ላይ እናተኩራለን። ለዚህ የገንዘብ ድጋፍ ከለየናቸው አንዳንድ ተነሳሽነቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

- በትምህርት ቤት ተቋማት ውስጥ የጤንነት እና የአቀባበል ጥረቶችን ማቀናጀትና የሰራተኞችን ፍላጎት መሠረት በማድረግ የጤንነት ፕሮግራሞችን ማስፋት።
- አዳዲስ ተነሳሽነቶችን ለመደገፍ፣ የሰራተኛ አመዳደብ ደረጃዎቻችንን ማሳደግ፣ ቡድኖቻችንን ማነሳሳትና የኮቪድ የደህንነት መስፈርቶችን ማቀፍ።
- የ ACPS ጥቅማ ጥቅም ፕሮግራም የተለያዩ ክፍሎች ላይ ቀጣይነት ያለው ግምገማ ለማካሄድ የሰራተኞች ጥቅማ ጥቅም ኮሚቴ ማቋቋም።
- ሁሉንም አዳዲስ ሠራተኞች በሥራ ላይ ባሉበት የመጀመሪያ ዓመት ውስጥ የሚደግፍ ሠራተኛን ወደ ስራ መስክ የማቀላቀል ፕሮግራም መቅረጽና ማቀናጀት።

- በተለያዩ ብዝሃነት ላይ ያተኮሩ ፕሮግራሞች አማካይነት ለምልመላ የሚሆን ሰፊ የአስተማሪ መስመር መዘርጋት።

ስለ ዕቅዶቻችን ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የእኛን የሰው ሃብት መምሪያ የማሻሻያ ዕቅድ ይመልከቱ።

## የትኩረት መስክ
# የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት

በአካል መማር የተሳለጠ ሽግግርን፣ በተማሪዎች ዕለታዊ የመማሪያ ተሞክሮ ውስጥ የቴክኖሎጂ ቀጣይነት ያለው ውህደት አስፈላጊ መሆኑን እና የሶፍትዌር ድጋፍ አገልግሎቶች ለሁሉም ትምህርት ቤቶች ዝግጁ መደረጋቸውን ለማረጋገጥ በመላው መምሪያችን ውስጥ የተስተካከለና ዘላቂ የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት እየገነባን ነው።

በሚቀጥሉት ወራት ውስጥ፣ ቡድናችን ተማሪዎች እንዳስፈላጊነቱ፣ በትምህርት ቤት እና በቤት ውስጥ የሚጠቀሙባቸውን መሳሪያዎች ለማቅረብ፤ ቤተሰቦች የፈለጉትን መዳረሻ እንዲያገኙ የ ወይፋይ እና የኢንተርኔት መዳረሻ እና ዕውቀትን ለማስፋት እና የቴክኖሎጂ ሀብቶችን ተደራሽ ለማድረግ የመረጃ ክፍለ ጊዜዎች/ዝግጅቶችን ለማቅረብ ቡድናችን በጀት መድቧል። በተቀናጁ ግንኙነቶች፣ በተሻሻለ የመረጃ ማጋራት፣ በአካል የድጋፍ መስጫ ሰዓቶች እና በተመሳሰሉ/ባልተመሳሰሉ ሙያዊ የመማር ዕድሎች አማካይነት የተማሪዎችን ማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና አካዳሚካዊ ፍላጎቶች በሚፈቱበት ጊዜ ለመምህራንና ለሰራተኞቻችን የምንሰጠውን ድጋፍ አጠናክረናል።

በ ESSER III ገንዘብ አማካይነት የት/ቤት መምሪያውን አሠራር ለማቀላጠፍና የበለጠ ተደራሽነትን እና ፍትሃዊነትን ለመደገፍ የሚያስችል አስተማማኝ፣ ሚዛናዊ እና ግልፅ የሆነ የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ማቅረብ እንችላለን። ለዚህ የገንዘብ ድጋፍ ከተመዘገቡት የተወሰኑ ናሙና ተነሳሽነቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡

- የግንኙነት ስርዓቶችን ማዘመን እና በሁሉም ት/ቤቶቸ ውስጥ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችን ደረጃ ማሳደግ።
- የሕንጻውን የ wifi መሳሪያዎች ደረጃ ማሳደግና እያረጁ ያሉ የፋይበር ኦፕቲክ የጀርባ አጥንትን በአዲስ በመተካት የበለጠ ፍጥነትና አዲስ የቴክኖሎጂ ደረጃዎች እንዲኖሩ ማገዝ።
- በመላው የትምህርትና የቢዝነስ ስራዎቻችን ውስጥ ያሉ ተጠቃሚዎቻችንን ለመደገፈ መሰረተ ልማቶቻችንን ማዘመንና ማቀናጀት።
- የቴክኖሎጂ ሰራተኞች ፕሮጀክቶችን ሲመሩና እነዚህን የደረጃ ማሻሻያዎች ሲተገብሩ እውቀታቸውን ማሳደግ።

ስለኛ የ 2018-2023 የቴክኖሎጂ ዕቅድ ተጨማሪ ያንብቡ።



# ራሳችንን ተጠያቂ ማድረግ

የእነዚህን ፕሮግራሞች ማቀድ፣ ማጥራት እና ተግባራዊ ማድረጋችን በሚቀጥሉት አራት ዓመታት ውስጥ ይቀጥላል። ለ**ግብ 4 ካለን ቁርጠኝነት ጋር በተጣጣመ መልኩ፡ ስትራቴጂክ የሐብት አመዳደብ**፣ የፋይናንስ አገልግሎቶች ሚኒስቴር የገንዘብ አጠቃቀምን ግልፅነት፣ ብቃትና ውጤታማነት ለማሳደግ ቁርጠኛ ነው።

በዕቅዶቻችን ላይ በተወሰነ ወቅት ግምገማ እናካሄዳለን፣ አስፈላጊ ሲሆንም ከማህበረሰብ ፍላጎቶች ጋር አግባብነት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ ክለሳዎች እናደርግበታለን። የሕግ ተገዥነትን ለመከታተልና የአሌክሳንደሪያ ከተማ ት/ቤት ቦርድ፣ የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ እና የዩናይትድ ስቴትስ የትምህርት ሚኒስቴርን ሪፖርት የማድረጊያ መስፈርቶች ለማሟላት የሚከተሉትን ሒደቶች ቀርጸናል።

### ተነሳሽነቶቻችንን ግልጽ ማድረግ

በዚህ ሂደት ውስጥ የመጀመሪያው እርምጃ እያንዳንዱን ተነሳሽነት በግልጽ ማሰቀመጥ፣ ባለቤትን መለየትና ከትግበራው ጋር የተያያዙ ወጪዎችን (ለምሳሌ፡ የተገዙ አገልግሎቶች፣ የተጨመሩ ሰራተኞች፣ የፋሲሊቲ ማሻሻያዎች፣ ወዘተ) በዝርዝር ማስቀመጥ ነው። ይህም የድጋፍ ገንዘብ ለማግኘት የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ የሚጠይቃቸውን የዕቅዱን የርዕስ ኮድ ደረጃ ዝርዝሮች ያቀርባል።

### ተጽእኗችንን መለካት

የ **ACPS 2025 እመርታን ለመከታተል ከሚተገበሩ ሂደቶች ጋር በመቀናጀት እኩልነት ለሁሉም**፣ የሐብት ክፍፍላችንን እና የገንዘብ ድጋፍ የምናደርግላቸው ፕሮግራሞች በቀጥታ ተማሪዎቻችን፣ ሰራተኞቻችን እና ማህበረሰቡ ላይ የሚያሳድሩትን ተጽእኖ የሚለኩ ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾችን (KPIs) እናዘጋጃለን። እራሳችንን ከምንጠይቃቸው ጥያቄዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡

- በትግበራችን ላይ እውቀትና መተማመንን ለመገንባት ክትትልን እንደ አጋጣሚ ልንጠቀም የምንችለው እንዴት ነው?
- የታቀዱ ፕሮግራሞቻችን እና ስትራቴጂዎቻችን በታማኝነት ሊተገበሩ ካልቻሉ ወይም የታሰበውን ተጽዕኖ ካላመጡ አካሄዳችንን የምንቀይረው እንዴት ነው?
- የተነሳሽነቶችን የገንዘብ ገደቦች እንዴት ልንከታተልና እና በአማራጭ ገንዘብ ለማብቃት ወይም ለማቆየት እቅድ ማውጣት የምንችለው እንዴት ነው?

### ሪፖርቶች

የተሻሻሉ የእመርታ ክትትል ሪፖርቶችን በየሩብ ዓመቱ ይፋ እናደርጋለን። ጥረቶችን በማህበረሰቦቻችን ውስጥ ላሉ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ለማሳወቅና ፍቺ ለመስጠት ጥረት በማድረግ ስራችን ለሁሉም ተደራሽ መሆኑ አስፈላጊ ነው።

### ሕዝባዊ መድረኮችና ሕዝባዊ ችሎቶች

የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ መስፈርቶችን ለማሟላትና ማህበረሰቡን ይበልጥ ለማሳተፍ እንዲቻል የ ESSER ዕቅዳችንን በየሩብ ዓመቱ እንከልሳለን። ACPS በኦክቶበር ወር ህዝባዊ መድረክን ያስተናግዳል (በመስከረም ወር የበጀት ቀን መቁጠሪያ ሲጸድቅ ትክክለኛው ቀን ይጠናቀቃል) በዚህም መድረክ ላይ የበጀት ሂደቱ ላይ በመወያየት በ ESSER እቅድ ላይ ወቅታዊ መረጃዎችን የምናቀርብበት ነው።

### ከሌሎች መምሪያዎች ጋር የሚደረግ ቅንጅት

የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ ከፌዴራል የወረርሽኝ እርዳታ የገንዘብ ድጋፍ ጋር የተያያዙ የተለያዩ የድጋፍ አገልግሎቶችን ይሰጣል። ቡድናችን በመላው ቨርጂኒያ ውስጥ ከሚማሩ ሌሎች አካላት ስለ ESSER ፈንድ አጠቃቀማቸው፣ ስለ ስኬታማ አሰራሮችና ተግዳሮቶችን ስለማሸነፊያ መንገዶች ለመማር በግዛት ደረጃ ተሳታፊ ይሆናል።

## የፈንድ ጊዜ ገደብ

በጉዟችን መጀመሪያ ላይ እንገኛለን፣ የ ESSER የገንዘብ ድጋፍ ለተለያዩ ዓመታትና የእኛ **ACPS 2025 ለሚቆየበት ጊዜ ዝግጁ ይሆናል፡ እኩልነት ለሁሉም**።

| | |
|---|---|
| ጁላይ 2021 | ረቂቅ እቅዱን ለማህበረሰቡ ማሳወቅ |
| ኦገስት 2021 | የሕዝባዊ ችሎት ሒደትን ማመቻቸት<br><br>የማህበረሰቡን ግብዓት በመጠቀም እቅዳችንን ማጠናቀቅ<br><br>የ ESSER III ፈንድ ማመልከቻዎችን ለ VDOE ማቅረብ |
| ሴፕቴምበር 2021 | ከ VDOE የገንዘብ እገዛ መቀበልና ሐብቶችን ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ፕሮግራሞች ማከፋፈል |
| ኦክቶበር 2021 | የቦርድ ወርክሾፕ እና የማህበረሰብ ውይይቶችን ማካሄደ |
| ኖቬምበር 2021<br>ዲሴምበር 2021 | እመርታን መከታተልና በመረጃና በግብረ መልስ ላይ በመመስረት ጉዞን ማስተካከል |
| 2022 - 2024 | በአራት ወር ጭማሪያችን ላይ ሪፖርት ማድረግና መከለስ |

## የአድናቆት ማስታወሻ

የአሌክሳንድሪያ ከተማ የህዝብ ትምህርት ቤቶች በትምህርት ቤቶቻችን ለሚማሩ፣ በከተማችን ለሚኖሩ እና ለሰፊው ሕዝብ ጥቅም ሲባል በትብብር የሚሰራ አሳቢ፣ ተቆርቋሪና ተሳታፊ ማህበረሰብ በመሆኑ ኩራት ይሰማዋል። ለአስተያየትዎ እናመሰግናለን፣ ሃሳቦችዎን ለመስማት እና ወደ **እኩልነት ለሁሉም** በሚወስደው ጎዳና እንድንቀጥል ስለሚረዱን መንገዶች ለመማር በጉጉት እንጠብቃለን።

በልዩ ሁኔታ የተጠራው የትምህርት ቤት የቦርድ ስብሰባ እና በ ESSER III ላይ የተጠራው ልዩ የሕዝባዊ ስብሰባ ኦገስት 3 ቀን ከቀኑ 7pm ይደረጋል። [እንዴት መሳተፍ እንደሚቻል ዝርዝር መረጃ ይመልከቱ]።